| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "ዐምሐራዊ ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2017-001 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |


# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

# ዐምሐራዊ ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ!



*"ዐምሐራ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የግብር ፡ ስሙ ፡ ነው ። "*
*ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ (ሊ. ፡ ጄኔ.) ።*

ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ይህን ፡ ሐሳብ ፥ ባስፈለገበት ፡ ኹኔታ ፡ ኹሉ ፥ ደጋግመው ፡ ተናግረውታል ፤ በተመሳሳይ ፡ ቃልም ፥ *"ዐምሐራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የፈረስ ፡ ስሙ ፡ ነው!"* ሲሉ ፡ ገልጸውታል ።

ዐምሐራነት ፡ እና ፡ ኢትዮጵያዊነት ፡ ያንድ ፡ ሳንቲም ፡ ኹለት ፡ ገጾች ፡ ናቸው ፤ አይለያዩም ። ይህ ፡ እውነት ፥ "በዱሮ ፡ ዘመን" ፡ ወይም ፡ ከኀምሳ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፥ ከሊቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ፥ ኹሉም ፡ የሚያውቀው ፥ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ጥርጣሬ ፡ የሌለበት ፡ እምነት ፡ ነበር ። የዘመኑ ፡ ሊቃውንት ፥ ከኪዳነ ፡ ወለድ ፡ ክፍሌ ፡ እስከ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፥ ከአድማሱ ፡ ጀንበሬ ፡ እስከ ፡ ዐያሌው ፡ ታምሩ ፥ ከሞገስ ፡ ዕቍበ ፡ እግዚእ ፡ እስከ ፡ ኤርሚያስ ፡ ከበደ ፥ ከነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ እስከ ፡ ጸጋዬ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፥ ኹሉም ፡ ሐሳባቸውን ፡ የደመደሙበት ፥ የሀገር ፡ ፍቅራቸውን ፡ ያሰሩበት ፡ ውላቸው ፡ ነው ።

"ዐምሐራ" ፥ ቃል ፡ በቃል ፥ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ይኸውም ፥ መብት ፡ እና ፡ ግዴታው ፡ በሕግ ፡ ተደንግገውለት ፡ እና ፡ ተጠብቀውለት ፥ ነጻነቱ ፡ የተረጋገጠለት ፡ የሀገር ፡ ሠሪ ፡ እና ፡ ባለቤት ፡ ሕዝብ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፈረንጆች ፡ "citizenry" ፡ ይሉታል ። "Citizen" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፥ ከየት-መጣው ፡ "City" ፡ እና ፡ "Denizen" ፡ ነው ። "City" ፡ ሀገር/ከተማ ፡ ማለት ፡ ሲኾን ፥ "Denizen" ፡ ደግሞ ፡ በአሮጌ ፡ ጀርመንኛ ፥ ነዋሪ ፡ ማለት ፡ ነው ። በተገናኝ ፥ Citizen ፡ ማለት ፥ ቃል ፡ በቃል ፥ የከተማ ፡ ነዋሪ ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። ዛሬ ፥ citizen ፡ የሚለው ፡ ቃል ፥ ከሥርወ-ቃሉም ፡ በላይ ፥ በዐያሌ ፡ የሥነ ፡ ግዛት ፡ ሊቃውንት ፡ እና ፡ ፈላስፎች ፡ ሐተታ ፡ ምክንያት ፥ እጅግ ፡ የከበደ ፡ እና ፡ የከበረ ፡ የረቀቀ ፡ ቃል ፡ ኾኗል ። "ነጻ ፡ ሕዝብ" ፡ የሚለው ፡ የዐምሐራ ፡ citizenry ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ትርጓሜ ፡ እና ፡ ትንታኔ ፣ ሐተታ ፡ እና ፡ አንድምታ ፡ ሳያሻው ፥ የሥነ ፡ ግዛት ፡ ምስጢሩን ፡ በቃሉ ፡ ሞልቶ ፡ ይገልጻል ፤ ሕዝቡም ፡ ስለ ፡ ምንነቱ ፡ አንዳች ፡ ጥርጣሬ ፡ ሳይገባው ፡ እና ፡ ማብራሪያ ፡ ሳይጠይቅበት ፡ በህልውናው ፡ ጥንትም ፡ ኖሮበታል ፥ ዛሬም ፡ ይኖርበታል ።

ከ 20 ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ አጋማሽ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣልያ ፥ በከፋፍለኽ ፡ ግዛ ፡ ስልት ፥ አለስሙ ፡ ስም ፡ ሰጥታ ፡ በዕብሪት ፡ "ዐምሐራ" ፡ ብላ ፡ በሰመየችው ፡ አካባቢ ፡ መነሻነት ፥ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ተፈጥሯል ። ዐምሐራ ፡ እንደ ፡ ከፊል ፡ ሕዝብ ፡ እንዲታይ ፤ የተገላቢጦሽም ፥ እንደ ፡ ጨቋኝ ፡ ወገን ፡ እንዲወገዝ ፡ የምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ በእጅ-አዙር ፡ በሚጨቀኑባቸው ፡ እና ፡ በአፍ-አዙር ፡ በሚሰብኩባቸው ፡ የጥፋት ፡ ኀይሎች ፡ ፀረ-ዐምሐራ ፡ ዘመቻቸውን ፡ አጧጡፈዋል ። ከኀምሳ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የጥላቻ ፡ ስብከት ፡ ሲቃጣበት ፡ የነበረው ፡ ዐምሐራ ፥ ከኀምሳ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ በለየለት ፡ ጦርነት ፡ በገዛ ፡ ሀገሩ ፡ ሲገደል ፡ እና ፡ ሲፈናቀል ፡ ኖረ ።

የዚህ ፡ ፀረ-ዐምሐራ ፡ ዘመቻ ፡ ግቦች ፡ ኹለት ፡ ናቸው ፦


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

1. ዐምሐራን ፡ ከሥልጣን ፡ ሰገነት ፡ ማባረር ፤
2. ዐምሐራን ፡ ከኢትዮጵያዊነት ፡ ማባድ ።

የፀረ-ዐምሐራው ፡ ዘመቻ ፡ የመጨረሻ ፡ ዐላማም ፡ ሀገር ፡ ሠሪውን ፡ ዐምሐራ ፡ ከሠራት ፡ ሀገሩ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመለየት ፥ መጋቤ-አልባ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ራሷን ፡ በራሷ ፡ እንድታጠፋ ፡ ማድረግ ፡ ይኾናል ።

ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ጦርን ፡ ደጋግሞ ፡ በማዝመት ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ የተሳነው ፡ የምልክዮሽ ፡ ኀይል ፥ በመጨረሻ ፡ የቀረው ፡ ዐቅድ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ አከፋፍሎ ፡ እና ፡ አጋዳድሎ ፥ በገዛ ፡ እጁ ፡ ሀገሩን ፡ እንዲያፈራርስለት ፡ ማድረግ ፡ ኾነ ። ዛሬ ፥ በዚህ ፡ በምልክዮሽ ፡ ፀረ-ኢትዮጵያ ፡ ዐቅድ ፡ አፈጻጸም ፡ ወቅት ፡ ላይ ፡ እንገኛለን ። መንደር-ገነን ፡ ኢሳይያስ ፡ አፈ-ወርቅ ፡ እና ፡ መንደር-ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ የዚህ ፡ ፀረ-ኢትዮጵያ ፡ ተልእኮ ፡ ቀንደኛዎቹ ፡ ፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

በረዥሙ ፡ ታሪካችን ፥ ከመቼውም ፡ ጊዜ ፡ በባሰ ፡ ፈተና ፡ ውስጥ ፡ ገብተናል ። ነገር ፡ ግን ፥ የፈተናው ፡ መባስ ፡ የድኅነታችንን ፡ መቅረብ ፡ የሚያመለክት ፡ እንጂ ፥ ጥፋታችንን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ አይኾንም ። በሥልጣኔ ፡ የተሠራ ፡ ሀገር ፡ በስይጣኔ ፡ ይፈርሳል ፡ ብሎ ፡ ማመን ፥ ጨለማ ፡ ብርሃንን ፡ ያሸንፈዋል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ማመን ፡ ያለ ፡ ዘበት ፡ ነው ።

ሀገር ፡ በተፈጥሮው ፡ መድኀኒቱን ፡ ያዘለ ፡ ኹነት ፡ በመኾኑ ፥ እንሆ ፥ ሀገር ፡ ኢትዮጵያም ፡ ብትጠቃ ፡ እና ፡ ህልውናዋ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ቢወድቅ ፥ ሀገራዊ ፡ መድኀኗ ፥ የዐምሐራ ፡ ፋኖ ፡ ተነሥቶ ፡ ታደጋት ።

የዐምሐራ ፡ ፋኖ ፡ የ"ዘር" ፡ ወይ ፡ የ"ፖለቲካ" ፡ ዐላማ ፡ የለውም ፤ አንድያ ፡ ዐላማው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ እግዚአና ፡ ማስከበር ፡ ነው ። በፋኖ ፡ ምራት ፡ ደረጃ ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ የሚታይ ፡ ስሕተትንም ፡ መጠለፍንም ፡ ጥፋትንም ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ርሱም ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣልያ ፡ በከለለችው ፡ ርኩስ ፡ ምኞታዊ ፡ "ክልል" ፡ ዐምሐራን ፡ የመከለል ፡ ፍላጎት ፡ ነው ። ይህን ፡ ባዕድ ፡ እና ፡ የተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ይዘው ፡ የፋኖ ፡ ምራት ፡ አባል ፡ ወይም ፡ መሪ ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ "ከስሕተታቸው" ፡ እንዲታረሙ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ መልክቱ ፡ ደርሷቸዋል ። የማይመለሱ ፡ ኾነው ፡ በስሕተታቸው ፡ ቢቀጥሉ ፡ ግን ፥ ብሎ ፡ ብሎ ፥ የትግሉ ፡ ወላፈን ፡ እና ፡ ትኵሳት ፡ ልክ ፡ ስለሚያገባቸው ፥ ለራሳቸው ፡ ሲሉ ፡ ይስተካከላሉ ፡ ብለን ፡ እናምናለን ።

ዐምሐራነት ፡ ሀገራዊነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ሀገር ፡ በሚሠራበት ፡ ርትዕ ፥ ባህሉም ፡ ቋንቋውም ፡ እምነቱም ፡ በዚሁ ፡ የርትዕ ፡ ጐዳና ፡ የተገኘ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማኅበረሰቦችን ፡ በውስጡ ፡ አዋሕዷል ። ሀገር ፡ የውዴታ ፡ ኅብረት ፡ ስለ ፡ ኾነችም ፥ ማንኛውም ፡ ሀገራዊ ፥ በተለየ ፡ ማኅበረሰባዊ ፡ ማንነቱ ፡ ሊታወቅም ፡ ሊኖርም ፡ ሊታይም ፡ ቢሻ ፥ ይህኑ ፡ ከማድረግ ፡ የሚከለክለው ፡ ሥርዐታዊ ፡ ማገጃ ፡ የለምና ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ዐያሌ ፡ ማኅበረሰቦችም ፡ ቋንቋዎችም ፡ ባህሎችም ፡ ተከብረው ፡ ይኖራሉ ።

ሀገራዊነት ፡ በርትዕ ፡ ሥርዐት ፡ ውስጥ ፡ ማደር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ሕዝቡ ፡ በትውልድም ፡ በባህልም ፡ በቋንቋም ፡ በእምነትም ፡ ተመሳስሎ ፡ በዐምሐራነት ፡ ተዋሕዷል ። ዐምሐራ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፤ የነገድ ፡ አባት ፡ የለውም ።

መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ በሀገራዊነቱ ፡ ዐምሐራ ፡ ኾኗልና ፥ በአንድ ፡ ልብ ፡ የዐምሐራ ፡ ፋኖን ፡ ትግል ፡ በመደገፍ ፡ እና ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱን ፡ በመመሥረት ፡—

- ሀገራዊ ፡ እግዚአናውን ፡ ያስከብራል ፥
- ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ይሠራል ፥
- ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥቱንም ፡ ያቆማል ፨

እግዚአናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ እናብር!

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።